# በትራንስፖርት ሚኒስቴር የተዘጋጀ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ የአፈፃጸም መመሪያ

# ቁጥር 687/2013

ሚያዝያ 2007 ዓ.ም

## መግቢያ

ትራንስፖርት ለአንድ አገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕድገት መሰረት የሆነና በህብረተሰቡም የኑሮ ዕድገት ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድርሻ ያለው መሆኑ የማይካድ እውነታ ነው።ከዚህ አንጻር በአገራችን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ የመንገድ ትራንስፖርት ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ የተሽከርካሪዎችን ምልልስ በማሳደግ የወጪና የገቢ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ወደብ እንዲደርሱና ከወደብ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ለተጠቃሚ ህብረተሰብ እንዲደርስ ለማስቻል የጭነት ትራንስፖርትን በህግና በሥርዓት እንዲመራ በኢ.ፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጠባቂነት ከታህሳስ 09/2006 ዓ.ም ጀምሮ የሚጸና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ የሚደነግግ አዋጅ ቁጥር 811/2006 ወጥቶ በሥራ ላይ ይገኛል።

የአዋጁን ዓላማ በአግባቡ ለማስፈጸም እንዲቻል ሁሉም አካላት የሚጠበቅበትን ግዴታ አውቆ እንዲፈጽም ለማስቻል በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 ሚኒስቴር ሚስሪያ ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 687/2013ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ የቃሉ አገባብና አጠቃቀም ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር ቀጥሎ የተጠቀሱት የቃላት ትርጓሜ በአዋጅ ቁጥር 811/2006 የተሰጡትን ትርጉም ይይዛሉ፣

   1. "አዋጅ" ማለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 811/2006 ማለት ነው።
   2. "የጭነት ማመላለሻ ተሽከርከሪ" ማለት ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርከሪ ሲሆን ጎታች መኪናን ይጨምራል።

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሰነድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

3. "ዕቃ" ማለት የቁም እንሰሳትን ጨምሮ ኮንቴነሮችን፣የዕቃ ማሻጊያዎችን ወይም ተመሳሳይ የዕቃ ማሸጊያ ቁሶችን ወይንም በዕቃ ላኪው ወይም በእቃ አስረካቢው በጥቅልና በፈሳሽ መልክ ለጭነት የሚቀርብ ማንኛውም ንብረት ነው።
4. "አጓጓዥ" ማለት ዕቃን በተሽከርካሪ አማካኝነት በየብስ ወይም በአገር ውስጥ ውሃ የሚያጓጉዝ ሰው ነው።
5. "ላኪ" ማለት ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገኖች ሲል ዕቃውን እንዲያጓጉዝ ለአጓጓዡ የሚያስረክብ ሰው ነው።
6. "ተረካቢ "ማለት ዕቃውን ለመቀበል ህጋዊ መብት ያለው ሰው ነው።
7. "መጋዘን" ማለት ማንኛውንም ብትንም፣ ጥቅልም ሆነ ፈሳሽ ዕቃዎችን በኮንቴነር ጭምር የመጫኛና የማራገፊያ የማከማቸት አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ቦታ ሆኖ ወደብንና የጉምሩክ መጋዘንን እንዲሁም የነዳጅ ማራገፊያ ቦታዎች ይጨምራል።
8. "የመጋዘን ባለቤቶች "ማለት የመጋዘኑ ባለንብረት ወይም መጋዘኑን በመከራየት የመጋዘን አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ማለት ነው።
9. "ባለሥልጣን" ማለት በትንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፣
10. "የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች" ማለት ትራንስፖርት ባለሥልጣን መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የከፈታቸው መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ተቆጣጣሪ አካላት ቁጥጥር የሚያደርጉባቸው ናቸው።
11. "አሽከርካሪ "ማለት የያዘውን የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን ለመንዳት የሚያስችለው ህጋዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የያዘ ሰው ነው፣
12. "ዲመሬጅ" ማለት የጭነት ተሽከርካሪን፣በላኪው፣ በተረካቢው፣ በመጋዘን ለመጫኛ ወይም ለማራገፊያ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ ወይም በመንግስት ተቆጣጠሪ አካላት ለሚካሄድ የቁጥጥር ሥራ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ እንዲቆይ በመደረጉ ለባከነው ጊዜ ማካካሻ የሚፈጸም ክፍያ ነው።
13. '' ተቆጣጣሪ አካላት'' ማለት በህግ በተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር በመግቢያ ወይም መውጫ በረ፣በመተላለፊያ መንገድ ላይ ወይም በማራገፊያ ወይም በመጫኛ ቦታዎች ወይም መጋዘኖች ዕቃን ወይም ጭነትን ወይም የቁም

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Transport

እንስሳትን በመሳሰሉት ላይ የፍተሻ ወይም የቁጥጥር ስራ የሚያከናውኑ አካላት ናቸው።

14. "ሰው "ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

15. "የፆታ አገላለጽ" በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴት ፆታንም ያጠቃልላል።

3 <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በጭነት ላኪዎች፣ተረካቢዎች፣ የመጫኛና የማራገፊያ አገልግሎት በሚሰጡ መጋዘኖች፣ የፍተሻና የቁጥጥር ሥራ በሚያከናውኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ በፋብሪካዎች፣በምርት አቅራቢዎች ፣ የደረቅና ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ አገልግሎት በሚሰጡ ተሸከርካሪዎችና አሽከርካሪዎች ፣ ባለተሸከርካሪዎች እና የጭነት ማኅበራት፣ድርጅቶች፣ ኩባንያዎችና አገልግሎቱን ባገኙ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

4 <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማ በጭነት ትራንስፖርት ቅልጥፍና ማነስና መዘግየት ምክንያት የሆኑ የአሰራር ችግሮችን በማስቀረት የጭነት ትራንስፖርት ምልልስን በማሳደግና አገልግሎቱን ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ወጪና ገቢ ምርቶች እንዲሁም ሌሎች ዕቃዎች በፍጥነትና በዝቅተኛ ወጪ ተጓጉዘው ለተጠቃሚው ወይም ለገበያ እንዲደርሱ በማስቻል የዲመሬጅ አዋጅን ተግባራዊ ማድረግ ነው።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

5 <u>የትራንስፖርት ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት</u>

በአዋጅ ቁጥር 468/1997 እና በአዋጅ ቁጥር 811/2006ዓ.ም የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

1. አዋጁና ይህ መመሪያ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

2. አዋጁን እና ይህን መመሪያ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ግንዛቤ ይሰጣል፣ አስፈላጊ የሆኑ የአሰራር ማንዋሎችን ያዘጋጃል፣ያሰራጫል። .
3. በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ዙሪያ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሔ ይሰጣል፣
4. የጭነት ተሽከርካሪዎች የጉዞ፣ የጊዜና የሥራ እንቅስቃሴ ስታንዳርድ ፣ ማኑዋል ያወጣል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
5. ለመመሪያው ተግባራዊነት በአስፈላጊ ቦታዎች የቁጥጥር ጣቢያዎችን በመክፈት አስፈላጊ ባለሙያዎችን ይመድባል፡
6. በየመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተቆጣጣሪዎችን በመመደብና ድንገተኛ ሱፐርቭዥን በማድረግ በመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች፣በመጋዘኖች በሚዛን መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተሽከርካሪዎች የገቡበትንና የወጡበትን ሰዓት ሞልተው መፈረማቸውን ያረጋግጣል፣
7. አጓጓዡ ከባለዕቃዎች የሚዋዋለውን የውል ሞዴልና የተለያዩ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የሚውሉ ፎርሞችን ያዘጋጃል ለሚመለከተው ያሰራጫል፣
8. በደረቅ ወደቦችና ሌሎች ቦታዎች ያለበቂ ምክንያት ተሽከርካሪዎች እንዳይቆሙና ወደ ሥራ እንዲገቡ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።
9. የተሽከርካሪዎች ያለሥራ መቆም መረጃን የሚመለከት ለሚፈልገው አካልና ፍትህ ሰጪ አካላት ለውሳኔ የሚረዳውን መረጃን ይሰጣል።
10. ይህንን መመሪያ እና አዋጁን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል፣

6 <u>የተቆጣጣሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የፍተሻና የቁጥጥር ሥራ የሚያከናውኑ ተቋማት የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖራቸዋል።

1. ፍተሻ እና ቁጥጥር በሚያከናውኑበት ጣቢያ በቂ የሰው ኃይል መመደብ፣
2. ለቁጥጥር ወይም ለፍተሻ የቀረበ ተሽከርካሪን በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ስታንዳርድ መሠረት ፈትሾ ወይም ተቆጣጥሮ መጨረስ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፣
3. የቁጥጥር እና የፍተሻ ጣቢያውን በአዋጁ መሰረት ለ24 ሰዓት ለሥራ ክፍት ማድረግ፤
4. ተሽከርካሪው ዕቃ ለማራገፍ፤ለመጫን፤ለቁጥጥር ወደ ጣቢያው(ቦታው) ደርሶ ከቆመበት ሰዓት አንስቶ የቆመበትንና የጨረሰበትን ሰዓት ሞልቶ በተዘጋጀው ፎርም ላይ በፊርማ ማረጋገጥ።
5. መረጃ ሲጠየቅ የዲመሬጅ አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰዱ እርምጃዎችን ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ሪፖርት ማቅረብ፤

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሰነድና ማኅደር አስተዳደር
ARCHIVE
Ministry of Trans

6. ትራንዚተሮች፣አሽከርካሪዎች፣የጭነት ባለቤቶች የተሟላ ሰነድ ሳያቀርቡ ወደ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እንዳይገቡ ማድረግ፣
7. ተሽከርካሪዎች ያለአግባብ በመቆጣጠሪያ ጣቢያና ቦታ ዕቃን ጭነው እንዳይቆሙ ክትትል በማድረግ ለትራንስፖርት ባለሥልጣን ሪፖርት ማድረግ።

## 7 የጭነት ትራንስፖርት የግል ባለንብረቶች፣ማህበራት፣ድርጅቶችና ኩባንያዎች(ኦፐሬተሮች) ኃላፊነትና ተግባር

የጭነት ትራንስፖርት የግል ባለንብረት፣ማህበር፣ድርጅትና ኩባንያ (ኦፐሬተር) የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

1. ትራንስፖርት ባለስልጣን የሚያዘጋጀውን የውል ፎርምና ቅፅ መረከብና ጥቅም ላይ ማዋል፣ ማንኛውንም ጭነት በውል ብቻ ማጓጓዝ፣
2. ወደ መጫኛ፣ማራገፊያ፣መቆጣጣሪያ ፣ደንበኛው የሚፈልግበት ቦታ አሽከርካሪው የደረሰበትን ሰዓት በተዘጋጀው ፎርም መሙላት የሚያስችል አሰራር መዘርጋትና ማረጋገጥ፣
3. የጭነት ተሽከርካሪው በጉዞ ላይ እያለ ከፍተኛ የቴክኒክ ችግር ቢያጋጥመው ለዕቃ ላኪ፣ተረካቢና መጋዘን ቤቶች ወዲያውኑ በማሳወቅ ሌላ ተሽከርካሪ በራሱ ወጪ በ100 ኪሎ ሜትር ርቀት ወሰን ውስጥ በ1 ቀን ስሌት ተተኪ ተሽከርካሪን ማቅረብና ጭነቱን ማጓጓዝ፣
4. ለጉዞው ቀናነት የሚያስፈልጉ ግብኣቶችን ማሟላት ፤
5. 24 ሰዓት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን በቂ የሰው ሀይልና አደራጃጀት መፍጠር፣
6. የተሽከርካሪውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ስልጣን ያለው አካል መረጃ ሲጠይቅ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ መስጠት፣
7. አጓጓዥም ሆነ የቁጥጥር ሥራን የሚያካሂዱ ተቋማት ያለአግባብ ተሽከርካሪን ላስቆሙበት ሰዓት በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ መ/ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
8. ተሽከርካሪው ወደ ማራገፊያ ቦታ ከመድረሱ በፊት ለንብረቱ ባለቤት ማሳወቅ፣
9. የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት አሽከርካሪነት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አሽከርካሪዎች በማህበራቸው ስለዲመሬጅ አዋጅ ደንብና መመሪያ ፣ቅጾችና ውሎች አተገባበር ላይ ግንዛቤ መስጠት።
10. አዋጁንና መመሪያውን ተግባራዊ ማድረግ፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE

## 8 . የአሽከርካሪ ኃላፊነትና ተግባር

አሽከርካሪ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖረዋል።

1. በፍተሻ፣ በቁጥጥር እና በመጋዘን ቦታዎች የደረሰበትንና አጠናቆ የወጣበትን ሰዓት ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ውልና ቅጽ መሠረት በቦታው ከተገኘው ተወካይ ጋር መፈራረም ፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው የሚመለከተው አካል የማይስማማ ከሆነ ልዩነቱን በሰነዱ ላይ አስፍሮ በአቅራቢያው ለሚገኘው የባለስልጣኑ ኢንስፔክተር ወይም ለህግ አካል ሪፖርት በማድረግ ማስፈረም
3. የሚፈለገውን መረጃ በተዘጋጀው የጉዞ መከታተያ ሎግ ቡክ መሠረት በአግባቡ እየመዘገበ መያዝ፣ ሲጠየቅም ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፣
4. የጭነት ተሽከርካሪው በጉዞ ላይ እያለ ከፍተኛ የቴክኒክ ችግር ቢያጋጥመው ለዕቃ ላኪ፣ተረካቢ እንዲሁም ለተቀጠረለት ድርጅት ወዲያውኑ በማሳወቅ ሌላ ተሽከርካሪ እንዲተካ ማድረግ፣
5. በተዘጋጀው የጉዞ ስታንደርድ መሠረት ተሽከርካሪውን ማንቀሳቀስ፣
6. ለሚጭነው ጭነት የተሟላ ሰነድ ፈርሞ መቀበልና አስፈርሞ መስጠት፣
7. ተሽከርካሪውን ውል ለተገባለት ሥራ ብቻ ማዋል፣
8. በተሽከርካሪው ላይ የተገጠመውን መገናኛ መሳሪያ በጥንቃቄ መያዝና መጠቀም፣
9. ጭነት የታሸገበት ማሸጊያ እንዳይፈታ ጥንቃቄ ማድረግ፣ከተፈታም ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ፣
10. በአዋጁ ከተቀመጠው ሰዓት በላይ ተሽከርካሪን ያስቆመ ሠራተኛ፣የዕቃ ባለንብረት፣ትርንዚተር፣ተቆጣጣሪ ተቋምን በዲመሬጅ ሕግ መሠረት ክፍያ የሚመለከተው አካል እንዲጠይቅ ማድረግ ።
11. ለተቆጣጣሪ መረጃ የመስጠት፣ የማስመዝገብ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፣
12. ተሽከርካሪው ወደ ማራገፊያ ጣቢያ ከመድረሱ በፊት ለሚመለከተው አካል(ለባለውሉ) ማሳወቅ።
13. የዲመሬጅ አዋጅና መመሪያውን ተግባራዊ ማድረግ፣

## 9. የዕቃ አስተላላፊ (የትራንዚተር) ኃላፊነትና ተግባር

የእቃ አስተላላፊ ወይም ትራንዚተር የሚከተለው ኃላፊነትና ተግባር ይኖረዋል፡-

1. የዲመሬጅ አዋጅና መመሪያን ተግባራዊ ማድረግ፣
2. ተሽከርካሪ በአዋጁ በተቀመጠው መሰረት ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ሙሉ ሰነድና መረጃ መስጠት ፣



ARCHIVE

3. ተሽከርካሪ በውሉ ወደ ተቀመጠው ቦታ እንደደረሰ በፍጥነት ዕቃውን ማስፈተሸና ለዚህም አስፈላጊውን ሰነድ ማቅረብ፣
4. በትራንዚተሩ ሊሟሉ የሚገቡ አስፈላጊ የትራንዚት መረጃዎችን በማሟላት ውል ፈጽሞ ጭነት ማጓጓዝ፣
5. ተሽከርካሪ እንዳይቆም በአዋጁ መሰረት 24 ሰዓት መስራት፣
6. አጋጋዡ ወይም ትራንስፖርተሩ ሚያጓጉዛው ጭነት በመጋዘን በመቆጣጣሪያ ጣቢያ እንዳይቆም ሙሉ ቅድሚያ ዝግጅት በማድረግ በወቅቱ ክፍያን በመፈጸም የማራገፍ ሥራን ሰነድ አሟልቶ መፈጸም፣በጊዜ ገደቡ ካልከተናወነ ለባከነው ጊዜ የዲመሬጅ ክፍያ መፈፀም፣
7. የማስተላለፍ ሥራን ለሚሰራው ተወካዩ ስለዲመሬጅ አዋጅና የአፈፃፀም መመሪያ ግንዛቤ መስጠት።

## 10. የመጋዘን ባለቤት ኃላፊነትና ተግባር

የመጋዘን ባለቤት የሚከተለው ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል።

1. በመጋዘኑ ክልል የደረሰውን ተሽከርካሪ የደረሰበትን እና አራግፎ ወይም ጭኖ የወጣበትን ሰዓት ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ሎግ ቡክና ተመሳሳይ ፎርም ላይ መፈረም፣
2. በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የማራገፍ አቅም ያለው በቂ የሰው ኃይል መመደብ፣
3. በቂ አደረጃጀት ፈጥሮ ቢሮውን 24 ሰዓት ለአገልግሎት ክፍት ማድረግ፣
4. ለትራንስፖርት ባለስልጣን ተቆጣጣሪ መረጃ መስጠት፣
5. በመጋዘን ባለቤት ምክንያት ለባከነ ጊዜ ለተገቢው አካል የዲመሬጅ ክፍያ መክፈል፣
6. ጭነት የማራገፍና የመጫን አገልግሎት ለሚሰጡ ሠራተኞቹ ስለዲመሬጅ አዋጅና መመሪያ ግንዛቤ መስጠት፤
7. የዲመሬጅ አዋጅ ተግባራዊ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ፈጣን አገልግሎት መስጠት

## 11. የዕቃ ተረካቢ ኃላፊነትና ተግባር

ዕቃ ተረካቢ የሚከተለው ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል።

1. ለሚረከበው ዕቃ በቂ ዝግጅት ማድረግ፣
2. የሚረከበውን ዕቃ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው የሎግ ቡክ ቅጽና ውል ላይ ከሕጋዊ ባለቤቱ ወይም ተወካዩ ላይ ፈርሞ መረከብ፣
3. ተሽከርካሪ ወደ ጭነት ማራገፊያ ቦታ ከመድረሱ በፊት በጭነት ማራገፊያ ቦታ በቂ የሰው ኃይል እና መሣሪያ የመሳሰሉትን አሟልቶ መጠበቅ፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

4. የጭነት ተሽከርካሪ በማራገፊያ ቦታ እንደደረሰ በአዋጁ በተወሰነው ሰዓት መሠረት ማራገፍ፣መረከብ፣ አጓጓዡ /አሽከርካሪው/ በሚያቀርበው የጉዞ ሰነድ ወይም የሥራ አፈፃፀም ሰነድ ላይ መፈረም፣
5. ጭነት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስፈልገውን የወደብ፣የጉምሩክ፣የባንክና ሌሎችም ፎርማሊቲዎች የጭነት ተሽከርካሪው ከመቅረቡ በፊት መጠናቀቁን ማረጋገጥ፣
6. በዕቃ አስተላላፊው ጥፋት ምክንያት ለተፈጸመ ቆይታ የዲመሬጅ ክፍያ መፈጸም፣
7. የዲመሬጅ አዋጅ እና መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ፈጣን አገልግሎት መስጠት፡፡

## 12. የዕቃ ላኪ ኃላፊነትና ተግባር

ዕቃ ላኪ የሚከተለው ኃላፊነትና ተግባር ይኖሩታል፡፡

1. ለሚልከው ዕቃ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት በመውሰድ ሰነዶችን አሟልቶ ማዘጋጀትና መላክ፣
2. የጭነቱ ዓይነት፣መጠን፣መነሻ እና መድረሻ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ቅጽና ውል መሠረት ከአጓጓዦች ጋር በመፈራረም ጭነቱ እንዲጓጓዝለት ማድረግ፣
3. ዕቃው ከመጓጓዙ በፊት በውሉ መሠረት ክፍያ መፈፀም፣
4. ጭነት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስፈልገውን የወደብ፣የጉምሩክ፣የባንክና የሌሎችም ፎርማሊቲዎችን የጭነት ተሽከርካሪ ከመቅረቡ በፊት መጠናቀቁን አረጋግጦ ተሽከርካሪ እንዲቀርብለት መጠየቅ፣
5. በጭነቱ መቀበያ ስፍራ በቂ የሰው ኃይልና የማራገፊያ መጋዘን፣መሳሪያ ማዘጋጀት፣
6. በአዋጁ ላይ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ተሽከርካሪን ካስቆመ ተገቢውን የዲመሬጅ ክፊያ በአዋጁ መሰረት በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ መፈጸም፣

# ክፍል 3
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 13. የዲመሬጅ ክፍያን ስለመጠየቅ

1. በአዋጁ ላይ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ተሽከርካሪን ያስቆመ ማንኛውም አካል የዲመሬጅ ክፍያ በአዋጁ መሰረት በሁለት ቀናት ጊዜ ውስጥ መፈጸም አለበት፣



የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሰነድና ማህደር አስተዳደር ARCHIVE

2. ማንኛውም አካል በቁጥጥር ሥራ መዘግየት ምክንያት ለትራንስፖርተሮች የከፈለውን የዲመሬጅ ክፍያ የቁጥጥር ሥራውን ካዘገየው አካል ክፍያውን መጠየቅ ይችላል፡
3. የዲመሬጅ ክፍያን በተመለከተ በዲመሬጅ ህጉ ከተቀመጠው ክፍያ ውጭ መቀነስ ወይም መጨመር አይቻልም።

14. **<u>ስለ ቅሬታ አቀራረብ እና ምላሽ</u>**

በዚህ መመሪያ አፈፃፀም ምክንያት ወይም ይህንን መመሪያ አስመልክቶ በሚሰጥ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ፣

1. በባለስልጣኑ በተዘረጋው መደበኛ የቅሬታ አቀራረብና አፈጻጸም ሥነ ሥረዓት መሰረት ቅሬታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በተፈጠረ በሦስት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ቅሬታውን በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል። ባለስልጣኑም የቀረበውን ቅሬታ ከሚመለከተው አካል በማጣራት በሦስት ቀናት ውስጥ መልስ ይሰጣል፣

2. ባለስልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለስልጣኑ ምላሽ በተሰጠው በአምስት ቀናት ውስጥ በፅሁፍ ማቅረብ የሚችል ሲሆን ሚኒስቴሩም ቅሬታው በቀረበለት በአምስት ቀናት ውስጥ ምላሹን ያስታውቀዋል፣

3. ባለስልጣኑ የሚቀርቡትን ቅሬታዎች ለመፍታት እንደአስፈላጊነቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቋቋም ይችላል።

15. **<u>ስለማስረጃ</u>**

1. የባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች በሌሉበት ስፍራ ተሽከርካሪው በሚንቀሳቀስበት አካባቢ የሚገኝ ማንኛውም ፖሊስ ወይም የጥበቃ አባል ወይም ከቀበሌ እስከ ክልል ያለ የአስተዳደር አካል ኃላፊ የተሽከርካሪው እንቅስቃሴ ላይ የሚፈርው ፊርማ ለዲመሬጅ ክፍያ ማስረጃ ይሆናል።
2. ከማስረጃው ትክክለኛነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ቅሬታ የሚያቀርብ ወገን ቢኖር ባለስልጣኑ በሚያደርገው ማጣራትና በሚደርስበት ውጤት ሊስተባበል ይችላል።

16. **<u>የሽከርካሪ መቆያ ጊዜ ሰዓት</u>**

የማንኛውም ተሽከርካሪ ለፍትሻ ወይም ለቁጥጥር ጣቢያ የቆመበት ሰዓት መቆጠር የሚጀምረው ወደጣቢያ ከመጣበትና ተራ ከያዘበት ሰዓት ጀምሮ ነው።

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Trans

17. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

18. **<u>መመሪያውን ስለ ማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሻሻል ይችላል ።

19. **<u>ተፈፃሚነት ስለሌላቸው መመሪያዎች</u>**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

20. **<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የሚያዝያ 2007 ዓ.ም

ወርቅነህ ገበየሁ
የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር

የትራንስፖርት ሚ...
ARCHIVE
Ministry of Tran...